በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት
የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቤተመዛግብትና ቤተመጻሕፍት ኤጀንሲ

**The Federal Democratic Republic of Ethiopia**

**National Archives and Library Agency**

# የአንጋፋ ሴት ደራሲያን መዝገበ የህይወት ታሪክ

***(Biographical Bibliography on Senior Women Authors)***

**ቅፅ 26፣ ቁጥር 2፣ 2001 ዓ.ም. Vol. 26 No. 2, 2008**

የሕትመት ማግኛና ዩኒየን ካታሎግ መምሪያ
በናሽናል ቢብሊዮግራፊ ቡድን ተዘጋጀ

**Prepared by**

**National Archives and Library of Ethiopia**

**Union catalogue and Acquisition Department**

**(National Bibliography Team)**

**November 2008/9**

**ታህሣሥ 2001**

**DECEMBER 2008**

# መግቢያ

በሀገራችን *የሴት ደራሲያን* ብዙም የሚታወቁ አልነበሩም፡፡ በሙያው ላይም ተሰማርተው ይገኙ የነበሩትም ሴቶች ሙያው እንደአሁኑ ብዙም በማይታወቅበት እጅግ በጣም ጥቂቶች ነበሩ፡፡

ወቅታዊ የሆኑ የስነ ጽሑፍ ውጤቶችን ለመላው ህብረተሰብ በማድረስ ሴት የመገናኛ ብዙሀን ባለሙያዎችና ሴት ደራሲያን ከፍተኛውን ሚና በመጫወት ላይ ይገኛሉ፡፡ ይህም የሴቶችን ዕኩልነት ብቻ ሳይሆን ሴቶች በማንኛውምና በየትኛውም ቦታ ላይ በመገኘት ከወንዶች እኩል ማንኛውንም ስራ መስራት እንደሚችሉ ከማየቱም በተጨማሪ የሴቶችን ችሎታና ብቃት በማሳየት ላይ ይገኛል፡፡

በመሆኑም የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቤተመዛግብትና ቤተመፃህፍት ኤጀንሲ በዚህኛው ዕትም ውስጥ ብዙም /ሁሉም/ ባይሆኑ የተወሰኑትንን በስነ ጽሑፍ በኩል ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደረጉና በማድረግ ላይ ያሉትን ***አንጋፋና ቀደምት የሴት ደራሲያንን*** ሥራዎቻቸውን በማስተዋወቅ ማንነታቸውና ሥራዎቻቸው ተረስቶ እንዳይቀር ሲባል ለትውለድ አቆይቶ ለማስተላለፍ እንዲቻል አጫጭር የህይወት ታሪካቸውን ከሥራዎቻቸው ጋር አዘጋጅቶ አቅርቧል፡፡

# <u>ማውጫ</u>

**አርዕስ** **ገፅ**

**1.** መግቢያ ………………………………………….……………. 2

2. አንጋፋ ሴት ደራስያን ………………………………………..4-28

ወይዘሮ ሮማነ ወርቅ ካሣሁን ከደረሷቸው መጻሕፍት አንዱን ሲመለከቱ ።



*የኢትዮጵያ ሴት ደራሲያን ማህበር ሚያዝያ 27 ቀን 1989 ዓ.ም. በ3 ሰዎች ማለትም በወ/ሮ ፊርማዬ ዓለሙ ፣ በወ/ሮ አረጋሽ ሰይፉ እና በወ/ሮ መቅደስ ጀምበሩ ተመሰረተ:: በ1993 ዓ.ም. መስራች ከሆኑት አንዷ ወ/ሮ ፊርማዬ ዓለሙ ከዚህ ዓለም በሞት ሲለዩ ወ/ሮ ሙሉ ሰለሞን የክበቡ ሊቀመንበር በመሆን በሁለት ተከታታይ ምርጫዎች በመመረጥ እስከ ጥር 7 ቀን 1998 ዓ.ም. ድረስ አገልግለዋል:: በመቀጠልም ወ/ሮ ውዳላት ገዳሙ ከጥር* 1998 *ዓ.ም. - ጥቅምት* 1999 *ማህበሩን አገልግለዋል። ከግንቦት 16 ቀን 1999 ዓ.ም. ጀምሮ ማህበሩ ወ/ሮ የምወድሽ በቀለን በመምረጥ ስራውን ቀጠለ::*

*የኢትዮጵያ ሴት ደራሲያን ማህበር ከክበብነት ተነስቶ ወደ ማህበርነት መሸጋገሩ በራሱ ትልቅ ነገር ነው:: ማህበሩ በስፖንሰር 4 መፃሕፍትን አሳትሟል::*

*እነሱም 1ኛ. ዕጣ የአሥር ሴት ደራሲያን ሥራዎችን የያዘ*

*2ኛ. ነፍስ የዘራች ሕይወት የደራሲ አማረች ተሰማን ስራ የያዘ*

*3ኛ. ከራስ ሽሽት የደራሲ ሶስና አሸናፊ ስራን የያዘ*

**4ኛ. ዕብዷ በለጠች የደራሲ የምወድሽ በቀለ ስራን የያዘ ሲሆን ማህበሩ ከእነዚህ በተጨማሪ ላለፉት አስርና አስራ አንድ ዓመታት በየሦስት ወሩ በሀገር ፍቅር ቲያትር ቤት ውስጥ « ግጥም በማለዳ » የተሰኘ ኘሮግራም አለው፡፡ የኢትዮጵያ ሴት ደራሲያን ማህበር በአሁኑ ስዓት 69 ሙሉ አባላት አሉት፡፡**



## ወ/ሮ ስንዱ ገብሩ /1908 - 2001/

ወ/ሮ ስንዱ ገብሩ ሸዋ መናገሻ ውስጥ አዲስ አለም ወረዳ ተወለዱ:: መጀመሪያ አባታቸው ከንቲባ ገብሩ ደስታ መምህር ቀጥረውላቸው እቤታቸው በኋላም በአዲስ አበባ የስዊድን ሚስዮን ትምህርት ቤት እስከ ስምንተኛ ክፍል ተማሩ:: በ1921 ዓ.ም. ወደ ስዊዘርላንድ ከዚያም ወደ ፈረንሳይ በመሄድ በተለያዩ ትምህርት ቤቶች ተምረዋል::

በ1925 ዓ.ም. ወደ አገራቸው ተመልሰው አዲስ አበባ ቅዱስ ጊዮርጊስ ትምህርት ቤት በመምህርነት ሰሩ:: በአምስቱ ዓመት የጣልያን ወረራ ጊዜ በአርበኝነት አገልግለዋል::

ከዚያም በተለያዩ የጣልያን እስር ቤቶች ታስረዋል:: ከነፃነት በኋላ በደሴ ወ/ሮ ስሂን ትምህርት ቤት፣ ቀጥሎ አዲስ አበባ እቴጌ መነን ትምህርት ቤት በዳይሬክተርነት ሰርተዋል:: በ1948 ዓ.ም. በፖርላማ የሕግ መምሪያ ምክር ቤት አባል፣ ከዚያም ለሁለት ዓመታት የሕግ መወሰኛ ምክትል ሊቀመንበር ቀጥሎም የኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ኘሬዚዳንት በኋላም በሕዝባዊ ኑሮ ዕድገት ሚኒስቴር በዋና ፀሐፊነትና በአስተዳዳሪነት ሰርተዋል::

ወ/ሮ ስንዱ ወደ ሥነ ጽሑፍ ዓለም የገቡት የውጭ አገር ታዋቂ ደራሲያንን ሥራዎች ለምሳሌ የሼክስፒርን፣ የሞሊየርን፣ የራስልን እና የሌሎችንም ሥራዎች በማንበብና ሳይታክቱ በመፃፍ ነው:: ለመጀመሪያ ጊዜ ያሳተሙት በ1942 ዓ.ም. «የልቤ መጽሐፍ» የተሰኘውን ድርሰታቸውን ነው:: በርካታ ግጥሞችና ተውኔቶች ጽፈዋል፣ ከፃፏቸው ውስጥ አብዛኞቹ አልታተሙም:: በ«እኛ» የግጥም መድብል ውስጥ ሰባት ግጥሞቻቸው ታትመዋል::



**ፈርማዬ አለሙ**

*ገጣሚ ፈርማዬ አለሙ ጥቅምት 27 ቀን 1948 ዓ.ም በሆሳዕና ከተማ ዘበኛ ሰፈር ተብሎ በሚታወቀው ስፍራ ተወለዱ:: ዕድሜያቸው ለትምህርት እንደ ደረሰ የአንደኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በጊምቢ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ደግሞ በሆሳዕና እራስ አባተና በልጅ አበበ ወ/ሰማያት ት/ቤት ተከታተለዋል::*

*ፈርማዬ በዕድገት በኅብረትና የዕውቀት የሥራ ዘመቻ በሐረር ከተማ ተሳትፈዋል:: ከዘመቻ መልስም በ1969 ዓ.ም. በካርታ ሥራ ድርጅት በሒሣብ ሠራተኛነት ተቀጥረው ሕይወታቸው እስካለፈበት ጊዜ ድረስ በተለያዩ የሥራ ክፍሎችና የኃላፊነት ቦታዎች ላይ አገልግለዋል::*

*ፈርማዬ ያላቸውን የሥነ ጽሑፍ ችሎታ በትምህርት ለማዳበር በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በማታው የትምህርት ክፍል በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ በ1987 ዓ.ም በዲኘሎማ የተመረቁ ሲሆን በ1988 ዓ.ም. ወደ ዩኒቨርስቲ በመመለስ በዲግሪ ለመመረቅ በዝግጅት ላይ ነበሩ::*

*ገጣሚዋ ለሥነ ጽሐፍ ችሉታቸው፣ በማሕበራዊ ጉዳዩች ላይ ባተኮሩ መጣጥፎች፤ እንዲሁም በልዩ የአቀራረብ ስልታቸው ዕውቅና አግኝተዋል:: ገጣሚ ፈርማዬ አለሙ በኢትዮጵያ ሬዲዮ በለገዳዲ የትምህርት ማሰራጫና በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን የተለያዩ ሥራዎቻቸውን በማቅረብ የሚታወቁ ከመሆኑም ባሻገር በተለያዩ መጽሔቶች ላይ ጽሑፎችን ያቀርቡ ነበር::*

*ፈርማዬ አለሙ በርካታ ጽሑፎችን ወደ ጥበብ መድረክ በማምጣት ከሌሎች አጋሮቻቸው ጋር በመሆን የሴት ደራሲያን ማህበር በማቋቋምና በማጠናከር ሕይወታቸው እስካለፈበት ጊዜ ድረስ የበኩላቸውን ድርሻ አበርክተዋል:: ማህበሩንም እስከ ጥር 1993 ዓ.ም. ድረስ በሊቀመንበርነት መርተዋል:: ፈርማዬ « ግጥም በማለዳ » የሚል ፕሮግራም የጀመሩ ብርቅዬ ባለሙያ ነበሩ::*

ከሴት ገጣሚያን ጋርም በመሆን በ1990 ዓ.ም « እኛ » የተሰኘ የግጥም መድብል ከታተሙ ስራዎቻቸው አንዱ ሲሆን በርካታ ያልታተሙ ሥራዎችም ነበራቸው። ፊርማዬ በአደረባቸው ሕመም በህክምና ሲረዱ ቆይተው በተወለዱ በአርባ አመታቸው ጥር 7 ቀን 1993 ዓ.ም. ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል።




**ሙሉ ሰለሞን**

ወ/ሮ ሙሉ ሰለሞን የኢትዮጵያ ሴት ደራስያን ማህበር ሊቀ መንበር በመሆን ለሁለት ተከታታይ ዓመታት በመመረጥ እስከ ጥር 7 1998 ዓ.ም. ድረስ አገልግለዋል። ለአንባብ ካቀረቡት የግጥም ስራዎቻቸው መካከል ‹‹ ስንክፍሬ››



**የምወድሽ በቀለ**

ወ/ሮ የምወድሽ በቀለ በአዲስ አበባ ተክለሃይማኖት አካባቢ ከአባታቸው ከአቶ በቀለ ወ/ገብርኤልና ከእናታቸው ከወ/ሮ ወርቅነሽ ወ/ማሪያም ነሐሴ 12 ቀን 1952 ዓ.ም. ተወለዱ። የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውን በአፍሪካ አንድነት ት/ቤት የ2ኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በቀድሞው ልዑል መኮንን በአሁኑ አዲስ ከተማ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ተከታትለዋል።

የምወድሽ በቀለ ከካምብሪጅ ዩኒቨርስቲ በተልዕኮ ትምህርት በፖብሊክ ሪሌሽን የመጀመሪያ ዲግሪ ያላቸው ሲሆን በማኔጅመንትና በጆርናሊዝም የተለያዩ የምስክር ወረቀቶች አግኝተዋል፡፡

የምወድሽ በቀለ በሥነ ጽሑፍ በኩል እስካሁን ካበረከቷቸው ውስጥ የሚከተሉት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

« አብዮታዊ ግጥሞች» 1971ዓ.ም. በተማሪነት ሕይወት፣ «የባከነ ጊዜ» አጭር ታሪክ በ1983 ዓ.ም.፣ «ያልፈራ ፍሬ» በ1991 ዓ.ም.፣ «ዕጣ» አጫጭር ትረካዎች /በቡድን/ በ1995 ዓ.ም.፣ «ዕብዷ በለጠች» በ1996 ዓ.ም.፣ «ያልተናበቡ ልቦች» /በቡድን / በ2000 ዓ.ም.

የምወድሽ በቀለ በአሁኑ ጊዜ የፖሊስና እርምጃው ጋዜጣ ዋና አዘጋጅነት በመስራት ላይ ይገኛሉ፡፡ በተጨማሪም የኢትዮጵያ ሴት ደራሲያን ማህበር ኘሬዚዳንትም ናቸው፡፡



**አበበች ድሪባ**

አበበች ድሪባ ኢረና በ1965 ዓ.ም. ከአባታቸው ከሻምበል ባሻ ድሪባ ኢረና ከእናታቸው ከወ/ሮ መድህኒት እርገጤ በአዲስ አበበ ከተማ ልዩ ስሙ ፈረንሳይ ለጋሲዮን በሚባል አካባቢ ተወለዱ፡፡

የ1ኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በመካነ ሕይወት 1ኛ ደረጃ ት/ቤት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በእንጦጦ አጠቃላይ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት በመከታተል በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን ከኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ አግኝተዋል፡፡ በፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲ በየሦስት ወሩ የሚታተመው « ሜሪት » መጽሔት ላይ በአዘጋጅነት ሠርተዋል፡፡ አሁን በአቅም ግንባታ ሚኒስቴር የህዝብ ግንኙነት ኤክስፐርት ሆነው በማገልገል ላይ ይገኛሉ፡፡

ፖፒሌሽን ሚዲያ ሴንተር ባዘጋጀው የሥነ ጽሑፍ ውድድር « ያልተናበቡ ልቦች» በሚለው አጭር ልቦለድ መድብል ውስጥ « ጫፍ ለመድረስ » በሚል ርዕስ አንድ አጭር ልቦለድ ጽፈው አሸናፊ ሆነዋል፡፡



**ሶስና አሸናፊ**

ሶስና አሸናፊ በ1965 ዓ.ም. በአዲስ አበባ ከተማ ራስ ደስታ ሆስፒታል አካባቢ ተወለዱ፡፡ የአንደኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በአፍሪካ አንድነት ቁጥር 2 እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በመድኃኒዓለም 2ኛ ደረጃ ት/ቤት አጠናቀዋል፡፡ ከዚህ ቀደም ፖፒሌሽን ሚዲያ ሴንተር ባሳተማቸው ሁለት መድብሎች ውስጥ አጭር ልቦለዶቻቸው ታትመውላቸዋል፡፡ በ1995 « ከራስ ሽሽት » በሚል ርዕስ የወጐች ስብስብ አሳትመዋል፡፡ በአሁኑ ጊዜ በኤፍ ኤም አዲስ 97.1 « ደወል » በተሰኘ ኘሮግራም አዘጋጅ ሆነው በመስራት ላይ ሲሆኑ በተጨማሪም « ኩኩ መለኮቴ » በተሰኘ ወርሃዊ መጽሄት አዘጋጅ ናቸው፡፡



**አረጋሽ ሰይፉ**

ወ/ሮ አረጋሽ ሰይፉ ከምባታ ውስጥ ተወለዱ፡፡ ከአንደኛ እስከ አምስተኛ ክፍል ድረስ እዚያው በሾኔ ት/ቤት ከስድስተኛ እስከ አስረኛ ደግሞ በጎጃም ጅጋ ፍኖተ ሰላምና ደብረማርቆስ ውስጥ ከተማሩ በኋላ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በአዲስ አበባ ተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት አጠናቀዋል፡፡ ኪዚያም በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በተከታታይ

*ትምህርት መርሀ ግብር በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ክፍል በዲኘሎማ ተመርቀው በቡናና ሻይ ባለሥልጣን በሕዝብ ግንኙነት ክፍል ውስጥም ሠርተዋል፡፡ የሴት ደራሲያን ክበብ መሥራችና ሊቀመንበርም ነበሩ፡፡*

*አረጋሽ ሃያ አምስት ግጥሞቻቸው መድብል ውስጥ ታትመውላቸዋል፡፡ በህይወት በቆዩባቸው ጊዜያት በተለያዩ መድረኮች ሥራዎቻቸውን አቅርበዋል፡፡ ህይወታቸው እስካለፈችበት ቀን ድረስ የኢትዮጵያ ሴት ደራሲያን ክበብን በሊቀመንበርነት መርተዋል፡፡*



**መቅደስ ጀምበሩ**

*መቅደስ ጀምበሩ የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በተወለዱበት ከተማ ደብረማርቆስ ንጉስ ተክለሃይማኖት ት/ቤት ከአጠናቀቁ በኋላ በ1977 ዓ.ም. አሥመራ ዩኒቨርስቲ ገብተው በሂሳብ መዝገብ አያያዝ በዲኘሎማ ተመርቀዋል፡፡ በ1999 ዓ.ም. ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በአካውንቲንግ የመጀመሪያ ዲግሪ አግኝተዋል፡፡ የሥነ ጽሑፍ ዝንባሌ አብሯቸው ያደገ ነው ፡፡ አምስተኛና ስድስተኛ ክፍል እያሉ ግጥም ያነቡ ነበር፣ ከፍ እያሉ ሲሄዱም ልቦለድ መፃህፍትን በማንበብ ስነጽሁፍን ማጣጣም ጀመሩ፣ የመጀመሪያ ግጥማቸውን የጻፉት የስምንተኛ ክፍል ተማሪ ሆነው ነበር፡፡ በዚያን ጊዜ መምህራን በርቺ ይሏቸው እንደነበር አሁን ድረስ ያስታውሳሉ፡፡ መቅደስ ከዚህ በፊት በ1984 ዓ.ም. /ንባስል/ በሚል ርዕስ ሰላሳ ዘጠኝ ግጥሞች ለአንባቢያን አቅርበዋል፡፡ /እኛ/ በተሸኘው መድብል ውስጥ ሃያ አራት ግጥሞቻቸው ታትመዋል፡፡ በመቀጠልም / ሙጋ/ የተሰኘ የግጥም ስብስብ አበርክተዋል፡፡*

*ከ1979 ዓ.ም. ጀምሮ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በመስራት ላይ ይገኛሉ፡፡*



**ዓለምፀሐይ ወዳጆ**

**ወ/ሮ ዓለምፀሐይ ወዳጆ የአንደኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በአዲስ አበባ ከተማ በፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ደግሞ በመድኃኒዓለም ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አጠናቀዋል:: በመቀጠልም በኢትዮጵያ ብሔራዊ ቴአትር የሁለት ዓመት የተውኔት ኮርስ ተከታትለዋል:: በብዙ ተውኔቶች ውስጥ በመሳተፍ በሙያቸው ታዋቂነትን አግኝተዋል:: « ለሥነ ጽሑፍ  ፍቅር ተገዥ ያደረጉኝም ሆነ ወደ ኪነጥበብ ዓለም የመሩኝ ብቁነቴንም በቅድሚያ የመሰከሩ መምህሮቼ » ናቸው የሚሉት ዓለም ፀሐይ በ1964 ዓ.ም. በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሥነ ጽሑፍ ውድድር አሸንፈዋል:: ብዙ ግጥሞችን በጋዜጦች ፣ በተለያዩ የብዕር ስሞች ጭምር ጽፈዋል:: የተወሰኑት ግጥሞቻቸውም በተለያዩ ድምፃውያን ተዜመዋል፣ በመድረክም ቀርበዋል:: በ1988 ዓ.ም « ማረፊያ ያጣች ሕይወት » በሚል ርዕስ ሃምሳ አምስት ግጥሞችን የያዘ መጽሐፍ በአሜሪካ አሳትመዋል:: « በእኛ » የግጥም መድብል ውስጥ ስድስት ግጥሞችን ለአንባቢ አቅርበዋል:: በቅርቡም በአሜሪካ የተለያዩ የግጥም ምሽቶችን በማዘጋጀት የሥነ ጽሑፍ ፍቅራቸውን በመወጣት ላይ ይገኛሉ::**



## ፀሐይ መላኩ

ወ/ሮ ፀሐይ መላኩ በ1946 ዓ.ም. በአዲስ አበባ ከተማ ተወለዱ፡፡ ለድርሰታቸው መነሻ የሆናቸውን ነገሮች ሲያብራሩ አባታቸው የቤተክህነት ትምህርት ስለነበራቸው መፃሕፍት ማንበብና መመርመር ይወዱ እንደነበርና እሳቸውም መንፈሳዊ ዕውቀት እንዲያገኙና የማንበብ ችሎታቸውንም እንዲያዳብሩ ያበረታቷቸው ነበር፡፡ በትምህርት ቤት መድረክ ግጥሞችንና አጫጭር ጽሑፎችን ያቀርቡ በነበረበት ወቅት ከጓደኞቻቸውና ከአስተማሪዎቻቸው ይሰጣቸው በነበረው የሞራል ድጋፍ የመፃፍ ፍላጎታቸው እያደገ እንደመጣ ይናገራሉ፡፡

ብሩሻቸውን ከቀለም ጋር ከሮቻቸውን ደግሞ ከጨርቅ ጋር በማገናኘት የሚፈጥሩት ሥነ ጥበባዊ ኑባሬ ከደራሲነታቸው በተጨማሪ ዘርፈ ብዙ ባለሙያ እንዲሆኑ አድርጓቸዋል፡፡ እያንዳንዱ ጊዜ የራሱ የሆነ የዘመን ትውስታ አለውና ልዩ ልዩ ፅሁፎችን ለማስረጃነት ሰብስቦ የመያዝ ልማድ አላቸው፡፡ ትርፍ የሚሉት አንዲትም ደቂቃ የላቸውም፡፡ እንያንዳንዷ የሕይወት ጉዞአቸው ከሥራ ጋር የተያያዘ ነው፡፡

በመምህርነት ከሦስት ዐሠርት ዓመታት በላይ አገልግለዋል፡፡ « ቋሳ »፣ በ1981 « አንጉዝ » በ1982 « ቢስራሄል » የተሰኙ ረጃጅም ልቦለድ መጽሐፍቶችን አሳትመዋል፡፡



**ከበደች ተክለአብ**

ወ/ሮ ከበደች ተክለአብ የተወለዱት በአዲስ አበባ ከተማ ነው ። ከአንደኛ እስከ ስምንተኛ ክፍል በወሰን ሰገድ ትምህርት ቤት ተምረው የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ደግሞ በልዑል መኮንን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አጠናቀዋል። ከ1966 እስከ 1968 ዓ.ም. በሥነ ጥበብ ትምህርት ቤት ተምረዋል። ከ1969 ዓ.ም. ጀምሮ ለአሥራ አንድ ዓመታት በሱማሊያ በእስር ቤት ቆይተዋል ። በ1981 ዓ.ም ከእስር ከተፈቱ በኋላም በ1983 « የትነው ? » በሚል ርዕስ አንድ የግጥም መጽሐፍ አሳትመዋል፡ ከዚህም ወደ አሜሪካ በመሄድ መጀመሪያ በፋይን አርትስ በማዕረግ የባችለር ዲግሪ ፣ ቀጥሎም በ1987 ዓ.ም. በዚሁ ትምህርት በማስተርስ ዲግሪ በማዕረግ ከሀዋርድ ዩኒቨርስቲ ተመርቀዋል። በሙያቸው በየጊዜው በአሜሪካ ውስጥ በተለያዩ ዩኒቨርስቲዎች እየተዘዋወሩ በጋራና በቡድን ኤግዚቢሽን ከማሳየታቸውም በላይ ልዩ ልዩ ጥናታዊ ጽሑፎችን አቅርበዋል። በአሁኑ ጊዜ በሜሪላንድ በሚገኘው ሞንትጎመሪ ኮሌጅ በማስተማር ላይ ይገኛሉ። በ « እኛ » መድብል ውስጥ ስድስት ግጥሞቻቸው ተካተዋል።



## ሸዋንግዟው በላይነህ

ወ/ሮ ሸዋንግዟው በላይነህ በ1953 ዓ.ም. « የህሊና ድጋፍ ምክር ከወቀሳ »፤ እንዲሁም « ጥንታዊው የሴቶች ሙያ » በሚሉ ርዕሶች ሁለት መፃሕፍት አሳትመዋል።

የሙያ መጽሐፍ በማሳተም ቀዳሚ ናቸው፡፡ የሚያውቋቸው ሰዎች በሕይወት አለመኖራቸውን ይናገራሉ፡፡



## የዝና ወርቁ

ወ/ሮ የዝና ወርቁ በ1954 በጎንደር ከተማ ተወለዱ፡፡ በ1978 ዓ.ም. ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ የባችለር ዲግሪያቸውን አግኝተዋል፡፡

በ1981 ዓ.ም. « የተሸጠው ሰይጣን » መጽሐፍ ውስጥ ኖቪላ / መካከለኛ የልቦለድ ሥራዎቻቸውን አሳትመዋል፡፡ « ያልተመቻት ችግኝ » በሚለው መጽሐፍ ውስጥም የአጭር ልቦለድ እና ኖቪላ ወጥተውላቸዋል፡፡ በ1996 « በክንፋም ህልሞች» መጽሐፍ ውስጥም አንድ አጭር ልቦለድ አውጥተዋል፡፡ « የአፍንጮ በር ወፎች » እና « ይቅርታ » - የሚሉ የልጆች መጽሐፍት በ2000 ዓ.ም. አሳትመዋል፡፡

## እመቤት ስጦታው

ወ/ሮ እመቤት ስጦታው በ1975 ዓ.ም. በአዲስ አበባ ከተማ ተወለዱ፡፡ የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በራስ አበበ አረጋይና በየካቲት 12 ትምህርት ቤቶች አጠናቀዋል፡፡ ከዩኒቲ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ በሴክሬታሪያል ሳይንስ ዲኘሎማ አግኝተዋል፡፡ በአሁኑ ጊዜ በአቢሲኒያ ባንክ በመስራት ላይ ይገኛሉ፡፡ « ቁም ነገር » እና « ጠብታ » ለተሰኙ መጽሄቶች አጫጭር ድርሰቶችን ያቀርባሉ፡፡

## ፅጌ አዳፍሬ

ወ/ሮ ፅጌ አዳፍሬ በ1956 ዓ.ም. « ሚዛን ተፈሪ የስንፍናና የክፋት መድኃኒት » እና « የፍቅር ጮራ የህብረት ከተማ » የተሰኙ መፃሕፍትን አሳትመዋል፡፡

**መርከብ ፀጋዬ**

መርከበ ፀጋዬ ደሴ ከተማ በ1967 ዓ.ም. ተወለዱ። የአንደኛ ደረጃ ትምህርታቸውን እዚያው ትግል ፍሬ ት/ቤት ፣ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ደግሞ በአዲስ አበባ ምስራቅ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አጠናቀዋል። በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በቆዩባቸው አመታት በሥነ ጽሑፍ መስክ በመሳተፍ የተለያዩ ግጥሞችንና አጫጭር ጽሑፎችን አቅርበዋል። የሥነ ጽሁፍ ዝንባሌ ያደረባቸው በደሴ ከተማ የላሊበላ የኪነት ቡድን ሲቋቋም መስራች ከነበሩት ከአባታቸው ከመምህር ፀጋዬ ሐይሌ መሆኑን ይናገራሉ። መርከብ፣ በተለይ በሥነ ግጥም እንዲገፉ ምክንያት የሆኗቸው አያታቸው እነደነበሩ ይናገራሉ።።። መርከብ « እኛ » በተሰኘው የጋራ መጽሐፍ ውስጥ 15 ግጥሞችን ለአንባቢያን አቅርበዋል።

**ሠናይት አበራ**

ሠናይት አበራ በ1968 ዓ.ም. በአዲስ አበባ ከተማ ተወለዱ። በተልዕኮ ትምህርት የቋንቋ ዲኘሎማ የተቀበሉ ሲሆን፣ በአሁኑ ጊዜ የአንድ መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ሥራ አስኪያጅ ናቸው። ሠናይት 25 ግጥሞችን « እኛ » በተሰኘው የግጥም መጻሕፍት ውስጥ አቅርበዋል።

**ስመኝ ግዛው**

ስመኝ ግዛው 1966 ዓ.ም. በአዲስ አበባ ተወልደው በአደጉበት አካባቢ በንፋስ ስልክ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን አጠናቀዋል። የመጀመሪያ ሥራዎቻቸው የሆኑትን 22 ግጥሞች ከጓደኞቻቸው ጋር በመሆን አሳትመዋል።

## ሮማን ታደሰ

ሮማን ታደሰ በ1969 ዓ.ም. በአዲስ አበባ ከተማ አራት ኪሎ አካባቢ ተወለዱ። የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በብሔራዊ ቤተመንግስት፣ በኮከበ ጽባህና በምኒልክ ትምህርት ቤቶች አጠናቀዋል። ከዚያም ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የሥነ ጥበብና ዲዛይን ትምህርት ቤት በግራፊክ ዲዛይነርነት በ1989 ዓ.ም. ተመርቀው በስአሊነት ለተለያዩ የመንግስትና የግል ድርጅቶች ሲሰሩ ቆይተዋል። ሮማን ከሚታወቁበት የካርቱን ስራ በተጨማሪም ለተለያዩ ጋዜጦች አጫጭር ድርሰቶችን በማቅረብ ላይ ይገኛሉ።

## *ሰአዳ መሐመድ*

ሰአዳ መሐመድ በ1969 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ ኮልፌ ተወለዱ፡፡ የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በአወሊያ ት/ቤት ካጠናቀቁ በኋላ በንግድ ሥራ ኮሌጅ ለአንድ ዓመት ያህል አካውንቲንግ ሲየጠኑ ቆይተው አጭር ጊዜ ስልጠና በመውሰድ በጋዜጠኝነት ሰርተዋል፡፡ « እፍታ » በተሰኘው መድብል አጫጭር ልቦለዶችና ግጥሞች ለንባብ ያበቁ ሲሆን በኢትዮጵያ ሬዲዮ ቅዳሜ የመዝናኛ ኘሮግራም ድራማዎችን አቅርበዋል፡፡ 1992 ዓ.ም. « እሾህማ ወርቅ » የተሰኘ ረዥም ልቦለድ ያሳተሙ ሲሆን በፖፐሌሽን ሚዲያ ሴንተር « ወንዞች እስኪሞሉ » መድብል ውስጥ « የወደቁት ዕንባ » የተሰኘውን አጭር ልቦለድ አቅርበዋል፡፡

## *መስከረም በቀለ*

መስከረም በቀለ የተወለዱት በ1965 አዲስ አበባ ከተማ ራስ ደስታ ሆስፒታል አካባቢ ነው፡፡ የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን የተማሩት በቀይ ኮከብና በመድኃኔዓለም ትምህርት ቤቶች ሲሆን በ1998 ዓ.ም. ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ የባችለር ዲግሪ ተቀብለዋል፡፡ « ሕይወት » በተሰኘ መጽሔት ላይ መንፈሳዊ ይዘት ያላቸው ድርሰቶችን አቅርበዋል፡፡ በጋዜጠኝነት ስራ ላይ የተሰማሩ ሲሆን ለሰባት አመታት ያህል « ሕያው ተስፋ » የሬዲዮ አገልግሎት ውስጥ ቤተሰብና ማህበራዊ ጉዳዮችን የሚዳስሱ ኘሮግራሞችን አዘጋጅተዋል፡፡

# ስለደራሲያኑ በጥቂቱ



ውዳላት ገዳሙ

**ፆ፡ለ**

ተውብትል አይሰማት - ምኑ እየቦረቀ፣
ሀመሟን ቁብ ሳይል - በጣሯ እየሳቀ፡፡
የእማማውን ወተት - የርሐቡን መጋኛ፣
ሰው የመሆናቸውን - የነፍሱን መዳኛ፡
ባልተወለደ አንጀት - ጨምቆ እያፈሰሰ፣
በሁለት እጆቹ - ጡቷን እያራሰ፣
ቁልቁል እየሳባት - እስከሚሆን አልቦ
'ሻሞ ይላቸዋል - ልጆችን ሰብስቦ፡፡

ጅ.ል



የሺወርቅ ወልዴ

**ተሸናፊ**

ስንቱን እንዳልጣለ
ጥሉ እንዳልፎከረ
ከራሱ ቢታገል
ተዘርሮ ቀረ፡፡



አበበች ድሪባ

## የልብ ወዳጅ

ስሜወት ዝም ብለው፣
ስስቅ ደብሯቸው፣
በማልቀሴ ሳቁ
ሐዘኔ ገብቷቸው::



ሶስና አሸናፊ

## ሴት አኩሪ

ሴት አኩሪ ተብላ
ምጣድ ላይ ከወጣች
በወጉ ሳታብጅ
ማሳመሩን ትታ
ሙልሙል ካሳረረች
ስያሚው በቀረ
ሹመት ባላገኘች::



ሶስና አሸናፊ

## ሴት አኩሪ

ሴት አኩሪ ተብላ
ምጣድ ላይ ከወጣች
በወጉ ሳታብጅ
ማሳመሩን ትታ
ሙልሙል ካሳረረች
ስያሜው በቀረ
ሹመት ባላገኘች።



ጽጌረዳ ኃይሉ

## ወዳጄ…

እንዳላጣህ ፈለግሁ
እንዳልፈልግህ ፈራሁህ
እናም
    አንድ ነገር ገባኝ
    መኖር ማለት
    የፈለጉትን የሚያጡበት
    የሚያጡትን የሚፈልጉበት።



ትዕግስት ምትኩ

## ?

የአዳም አፈጣጠር
መሆኑን ከአፈር
ደግሜ፣ደግሜ፣ደጋግሜ ሰማሁ
ከሱ ግራ አጥንት እኔ እንደተሰራሁ::
ግና...
እኔን የገረመኝ መልስ ያጣሁለት
አዳምን ሲቀጣ በእጅጉ ሲያዝንበት
አፈር ነህና... ብሎ ሲፈርድበት፣
ታዲያ...
ተዘንግቶ ይሆን ከአጥንቱ እንደሠራኝ
ከአፈር ሳልፈጠር አፈር የሚያስበላኝ?



ምሥራቅ ተረፈ

## ትል

አበሻ የነደደው ዕለት
ደርሶ ከሰው ሲጣላ
ሲተናነቀው ድንፋታ
እልህ ደሙ ሲፈላ
አፉን ከፈተ ሊሳደብ
ሂድ ትል አለ
ትልን አርክሶ
ትሉ ባመረተው ሀር
እስካርፍ ሽሚዙን ለብሶ::



ታየች ወልደማርያም

## ምን ነካኝ

ምን ነካኝ!
ሆዴን! ቆረጥ! ቆረጥ
ደሞ ቆንጠጥ ቆንጠጥ!
ደሞ ፈረገጥ ፈርገጥ!
እያለ እስቸገረኝ፣
በርበሬ ያጣው ትል
አደገ መሰለኝ፡፡



አዚብ ዮሴፍ

## የከብቶች አለቃ

በእግዜርኛ ቋንቋ ሰላምታ ብሰጠው፣
አልጥም አለውና ቃል ቢጎረብጠው፡፡
« ሃይ! » ብሎኝ አለፈ በከብትኛ ቋንቋ፤
ዘመነኛው ጓዴ የከብቶች አለቃ፡፡



ምህረት ከበደ

## እኔና ሃገሬ

እንዲህ ነኝ አንዲያነኝ ... ማለት አፈር በላ
ስሜ ባንቺ ጉያ ሙጥኝ ... ተጠቅልላ
አንቺ የፊት መቅረዝ ... እኔ ያንቺ ጥላ
ሀገሬ ... ሀገሬ ...ጉድ ነው ያንቺስ ገላ
በትንሿ ልቤ ... ነፍሴ አንቺን አዝላ
ባንድ ርምጃ ርቀት ከፊትሽ ብከላ
ስምሽ ተዝረከርኮ...ስሜን ገፎ በላ፡፡



# የምወድሽ በቀለ

**ለመኖር**

ውስጤ እየነፈረ ከንፈሬ ገልጬ
ለይምሰል ለታይታ በዐይኔ ቀላውጬ
ልኖር እስቃለሁ በቀን ተወሽቄ
ዕድሜ ለጥርስ አምላክ ላስመሳዩ ሳቁ፡፡



ሜሮን ጌትነት

## አታጨብጭቡ

'በላች' አላችሁኝ
እጆቼ ሳይነኩ እናንተ አጉርሳችሁ
'ደረሰች' ተባልኩኝ
መሮጥ ሳያቅተኝ በእቅፍ ወስዳችሁ
ከእንግዲህስ በቃ!
'ቆመች 'አትበሉኝ
እኔ መርገጥ ስችል እየደገፋችሁ
'አይታለች' አትበሉ
ማየት ሳይሳነኝ እየጠቆማችሁ
ይልቅ ክብረት ጭሬ
ውሃ ሲፈልቅልኝ ያለ ናንተ ድጋፍ
ባህርዛፍ ተክዬ
እንጀራ ሲያፈራ ያ የተከልኩት ዛፍ
ያኔ 'ሰራች!'በሉ
ስሜን በፈጠራ ዘክሩ ከተቡ
ዛሬ ግን በባዶው
ምንም በሌለበት ለኔ አታጨብጭቡ።

